# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 148 መጋቢት 8 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

… በውጭ አገራት ያለው ኢትዮጵያዊ ግን አመጹን አሁኑኑ በያለበት አገር ውስጥ ሆኖ ለመጀመር የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት ለአፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ህዝቦች ከነፃነት ይልቅ መረጋጋትን በመፈለግ ከአምባገነን ገዢዎች ጎን በመቆማቸው የዲሞክራሲ እጦት በህዝቦች ላይ ያስከተለው ምሬት በገዛ ዓይኖቻቸው ለማየት ችለዋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ ከወጣን ገና 10 ወራችን ነው ስለዚህ የቱኒዚያው አይነት አብዮት በአገራችን ሊከሰት አይችልም አለ

ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 3 ቀን በወያኔ ቁጥጥር ሥር ላሉት የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠው የወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በህዝብ ምርጫ ሥልጣን ላይ ከወጣን ገና 10 ወራችን ስለሆነ ህዝቡ በአመጽ ከሥልጣን ሊያስነሳን ምንም ምክንያት የለውም ሲል የቱንዚያው አይነት ህዝባዊ አመጽ በአገራችን ሊፈንዳ እንደማይችል እርስ በርሱ በሚቃረን ቋንቋ መግለጹ ታውቋል።

ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በከፍተኛ ስጋት እና መረበሽ መንፈስ ውስጥ ሆኖ መግለጫውን የሰጠው መለስ ዜናዊ ምንም እንኳ ህዝባችን በምርጫ የሰጠንን የ5 አመት ኮንትራት በሰጠን በ10 ወራት ዕድሜ ውስጥ በአደባባይ ነውጥ ሊቀማን ይችላል ብለን ማሰብ ባንችልም፤ ሻቢያ ያደራጃቸውን አክራሪ ተቃዋሚዎች በማሰማራት የአደባባይ ነውጥ ማስነሳቱ እንደማይቀር ሰሞኑን "አዲስ አበባን ሌላኛው ባግዳድ አድርጋታለሁ"ብሎ እየሰጠ ካለው ዛቻ እና ድንፋታ መረዳት ይቻላል በማለት ብዙዎችን ፈገግ ያደረገ ውንጀላ አቅርቧል። ኮሎኔል ጋዳፊ በአገራቸው ውስጥ የተነሳውን ህዝባዊ አመጽ "አልካይዳ ያደራጀው ነው " በማለት የምዕራቡን ድጋፍ ለማግኘት እንደሞከሩት ሁሉ፤ ዘረኛው መለስ ዜናዊም "ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ባላንባ ነኝ" እያለ ላልፉት 10 አመታት ዘመቻ የሚያካሂድባትን ኤርትራ ለመወንጀል መዳዳቱ ግለሰቡ የገባበትን ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና መረበሽ ያመለክታል ሲሉ ቃለመጠይቁን የተከታተሉት ሰዎች ይናገራሉ።(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ ኢሳትን ከአየር ለማውረድ ከፍተኛ የሆነ ዘመቻ ላይ እንደሚገኝ የግንቦት 7 ምንጮች ገለጹ

ነጻ የሆነ የመረጃ ፍሰትን በመቆጣጠር የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም እየባዘነ ያለው ዘረኛው የወያኔ ሥርዓት የሰሜን አፍሪካ ህዝባዊ አብዮት በአገራችን ውስጥ የፈጠረውን ህዝባዊ መነሳሳት በመፍራት ኢሳትን ከአየር ለማውረድ ይቻለው ዘንድ የገንዘብ ፤ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ሃይል ሊያስገኝ በሚችለው አቅም ሁሉ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ለወያኔ ቅርበት ያላቸው የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

በከፍተኛ ብሶትና ጭንቀት ውስጥ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደብቸኛ የመረጃ ምንጭ እያገለገለ ያለው ኢሳት ወያኔ የተዘፈቀበትን ሙስና ፤የሃብት ዘረፋና የሥልጣን ብልግና እየተከታተለ በማጋለጥ ሥራ ላይ ከመጠመዱም በላይ የመለስ ዜናዊ ሚስት የሆነቺው አዜብ መስፍን በዱባይ እና የፓሪስ ውድ ሸቀጣሸቀጥ መደብሮች እየበተነች ያለቺውን የአገሪቱን ሃብት ለህዝብ አይንና ጆሮ በማድረሱ መለስ እና ግብረአበሮቹ ሊወጡ በማይችሉት ቅለት ውስጥ እንደከተታቸው ይህም አገዛዙን ክፉኛ እንዳስቆጣ የመረጃ ምንጮቻችን ተናግረዋል። በዚህም የተነሳ "በቀላሉ ልንመከተው የማንችለው ህዝባዊ ቁጣ ከመቀስቀሱ በፊት የሚያስከፍለው ዋጋ ሁሉ ተከፍሎ ኢሳት በአስቸኳይ ከአየር መውረድ አለበት የሚል ትዕዛዝ በቀጥታ ከመለስ ዜናዊ መሰጠቱንና ተግባራዊ እንቅስቃሴም እንደተጀመረ አክለው አጋልጠዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ የሰሜን አፍሪካን አይነት አብዮት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊያነሳሱ ያሴራሉ በሚል ክስ በርካታ ወጣቶችን ማሰር እንደቀጠለ ነው።

### የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዋና ጸሃፊ ከ40 በላይ አባላቶቻቸው መታሰራቸውን ገለጹ

የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሰሜን አፍሪካው አይነት ህዝባዊ አመጽ ሊነሳብኝ ይችላል ከሚል ፍርሃት በርካታ ወጣቶችን በሰበብ አስባብ እያሰረ እንደሚገኝ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት አዲስ አበባን ጨምሮ ባሉት ትላልቅ ከተሞች ብዛት ያላቸው የደህንነትና የፌደራል ፖሊስ አባላት ከመመደባቸውም በላይ ወያኔ ባሰማራቸው ፖሊሶችና የደህንነት ሠራተኞች ካለመተማመን ይመስላል የህወሃት አባላት የሆኑት ታማኝ ወጣቶች ከትግራይ ክልል ተመልምለው በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ተበትነዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ የኦሮሞ ኮንግረስና የኦፌዲን አመራር አባላት በየግል ለኢሳት በሰጡት መረጃ ከ40 በላይ አባላቶቻቸው ባለፉት 3 ቀናት ውስጥ መታሰራቸውንና አንዳንዶቹ ፍርድ ቤት ቀርበው የቱንዚያን አይነት ህዝባዊ አብዮት ለመቀስቀስ ትንቀሳቀሳላችሁ በሚል ክስ መወንጀላቸውን፤ የተቀሩት ግን የት እንዳሰሩዋቸው እንኳን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዓለም ለአምባገነኖች የነበረው ትእግስት መሙዋጠጡን ገለጹ

ከቱኒዚያ ተነስቶ በተለይም የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን የለበለበው ህዝባዊ ማእበል የበርካታ ሃገራትን በር ማንኳኳት ከጀመረ ወዲህ ዓለማቺን ለአምባገነኖች የነበራት ትእግስት አልቆ እንጥፍጣፊ ብቻ እንደቀራት የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ ር ብርሃኑ ነጋ ገለጹ፣ ፤ ዶ ር ብርሃኑ ነጋ ይህን የተናገሩት ባለፈው ቅዳሜና እሁድ መጋቢት 2 እና 3 ቀን 2003 ዓም በስቶክሆለም ስዊድንና በኦስሎ ኖርዌይ ተገኝተው ከኢትዮጵያዊያን ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ባደረጉበት ውይይት ወቅት መሆኑን ዘጋቢያችን ከኦስሎ ባስተላለፈልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

ዶ/ር ብርሃኑ በሁለቱም አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር በያንዳንዱ ከአራት ሰአት በላይ የፈጀ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ለውይይት መነሻ ያቀረቡት ጽሁፍም በቃ ገሞ የሚል እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ገልጿል። ዶ/ር ብርሃኑ ይህን ርእስ ለውይይት መንሻ እንዲሆን የፈለጉበት ዋና ምክንያት ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ሆን ተብሎ ማህበረሰባችንን ለመከፋፈል የሚፈለገውን ነገር አንድ ሆነን በአንድ ቃል መነሳት እንደምንችል ለማሳየት እንደሆነ ለተሰብሳቢዎቹ ገልጸዋል።

ዛሬ ስለ ኢትዮጵያ አበሳ ማውራት ራሱን የቻለ ስራና ጊዜንም የሚወስድ ነው ያሉት ዶ/ር ብርሃኑ በሰሜን አፍሪቃ የታየው ክስተት እኛንም እንደሚነካና ያለንበት ወቅትም የአብዮት እንደሆነ ገልጸው ከኢትዮጵያዊያኑ ጋር ለመወያየት ያነሱት ነጥብ ቀደም ብሎ በዳላስና በሂዩስተን የቀረበ ሃሳብ ቀጣይ ክፍል እንደሆነ ገልፀዋል። ዶ/ር ብርሃኑ ቀደም ብሎ በዳላስና በሂዩስተን ኢትዮጵያዊያን ከሰሜን አፍሪቃው አብዮት ልንማራቸው ስለሚገቡ ሶስት ነገሮች በሚል ርእስ ባደረጉት ንግግር የነጻነትና ዴሞክራሲ ፍላጎቶች የሰው ልጆች ሁሉ የሚፈልጓቸው እሴቶች መሆናቸው መረጋገጡን፤ የሰሜን አፍሪቃ አብዮቶች አፍሪቃዊያን በራሳቸው ያላቸውን መተማመን አጉልቶ ያወጣና አፍሪቃዊያንም የስ ዋ ካን ያሉበት እንደነበር እንዲሁም ወቀቱ አፍሪቃዊያን የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን የተነሱበት አጋጣሚ በመሆኑ ነጻነት ወይም ሞት ብለው ፊት ለፊት መጋፈጣቸውን መግለጻቸውን አውስተዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአውሮጳ ፓርላማ የኢትዮጵያን ጉዳይ አስመልክቶ ስብሰባ አደረገ

አለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሂውማና ራይትስ ዎች በግርድፍ ትርጉሙ "ነጻነት አልባው ልማት" ፡የርዳታ ገንዘብ አፈናን ለማጠናከር ሲውል Development without Freedom; How aid underwrites repression in Ethiopia በሚል ርዕስ ያወጣውን ሪፖርት አስመልክቶ ሁለት የአውሮፓ ህብረት ኮሚቴዎች ማለትም "የሰብአዊ መብት ኮሚቴ እና የልማት ኮሚቴ" በእንግሊዚኛው አጠራር Sub commitee on Human Rights and Committee on Devlopment ) የተባሉት ኮሚቴዎች በጥምረት ያዘጋጁት ስብሰባ መጋቢት 5 ቀን 2003 አም በአውሮፓ ፓርላማ ውስጥ መካሄዱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከብራስልስ ቤልጅዬም በላከልን ዘጋባ ገለጸ ።

የቀድሞው የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን የልማት ኮሚሽነር የነበሩት ሚስተር ሉዊ ሚሼል እና በምርጫ 97 የአውሮፓ ምርጫ ታዛቢ ቡድን መሪ የነበሩት ክብርት አና ጎሜዝ በተሳተፉበት በዚህ ስብሰባ ላይ ሂውማና ራይትስ ዎችን በመወከል ሚስተር ቤን ራወለንስ ባቀረቡት ሪፖርት የቻይናው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአዲስ አበባ አውራ መንገዶችና አደባባዮች በከፍተኛ የፖሊስ እና ፀጥታ ጥበቃ ሥር መሆኑ ታወቀ

ሰሜን አፍሪካንና መካከለኛውን ምስራቅ እያዳረሰ ያለው ህዝባዊ አብዮት ሊፈነዳ ይችላል የሚል ፍርሃትና ስጋት ሰንጎ የያዘው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በአዲስ አበባ ትላልቅ መንገዶችና አደባባዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የጥበቃ ቡድን እንዳሰማራ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

ባለፈው ረቡዕና ሃሙስ በአገራችን መዲና በአዲስ አበባ የተካሄደው አፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት ጀምሮ የወታደርና የፖሊስ ልብስ የለበሱ በርካታ አባላት በተለያየ የከተማው መንገዶችና አደባባዮች ላይ በመሠማራት የእያንዳንዱን ሰው እንቅስቃሴ በቅርብና በሩቅ ሲከታተሉ እንደነበረ የታወቀ ሲሆን ጥበቃው በመዲናችን የተሰባሰቡትን አምባገነኖች ድህንነት ከመጠበቅ ያለፈና ወያኔ ያለበትን ጭንቀት አመልካች እንደሆነ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስገልጹ ስንበተዋል እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት።

ላለፉት 20 አመታት በህዝባችን ላይ የደረሰው ግፍና መከራ በከተማው ውስጥ በተገነቡት ህንጻዎችና በአለም አቀፍ ህብረተሰብ የገንዘብ ድጋፍ በተዘረጉ አስፋልት መንገዶች ውዳሴ እንዲደበሰበስ በፕሮፖጋንዳ ዜናችን የሚያደነቁረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቱንዚያና በግብጽ አምባገነኖችን አከርካሪ የመታ ህዝባዊ አብዮት አይነት በአገራችን ለመነሳት ምንም አይነት ነባራዊ ተጨባጭ ምክንያት የለም ከማለት አልፎ ከሁለቱ አገሮች የተሻለ ፍትህ እና የዜጎች እኩልነት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የማጥቃት ዘመቻ አሁኑኑ ይጀምሩ!!!

በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን "አምባገነኖችን እየናጠ ያለው ህዝባዊ ማዕበል ወደ አገራችን መቼ ይደርሳል?" በሚል ጉጉት ውስጥ ናቸው። ይህ ጉጉት ተገቢም፤ የሚጠበቅም ነገር ነው። በዚህ ጉጉት መነሻነትም ከየአቅጣጫው የተለያዩ መልእክቶችንና ጥሪዎችን እንሰማለን።

ህዝባዊው አመጽ አገራችን ውስጥ የሚጀመርበት ሁኔታ በአብዛኛው አገር ውስጥ ባሉ ሁኔታዎች የሚወሰን ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ ብለን እናምናለን።

በውጭ አገራት ያለው ኢትዮጵያዊ ግን አመጹን አሁኑኑ በያለበት አገር ውስጥ ሆኖ ለመጀመር የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት ለአፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ህዝቦች ከነፃነት ይልቅ መረጋጋትን በመፈለግ ከአምባገነን ገዢዎች ጎን በመቆማቸው የዲሞክራሲ እጦት በህዝቦች ላይ ያስከተለው ምሬት በገዛ ዓይኖቻቸው ለማየት ችለዋል።

የሰሜን አፍሪቃና መካከለኛ ምሥራቅ አብዮቶች ምዕራባዊያን መንግስታትን፤ ታዋቂ የሆኑ የአውሮፓ ተቋማትና ግለሰቦችን ለቅሌት ዳርጓቸዋል። ምሁራንና የቢዝነስ ሰዎች ብቻ ሳይሆን የኪነጥበብ ሰዎችም ጭምር ከአምባገነኖች ጋር በፈጸሟቸው ኮንትራቶች ያገኙትን ትርፍ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሰጡ ግፊት እየተደረገባቸው ይገኛል።

በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ይህን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ቀንደኛ ደጋፊዎች የሆኑትን ምዕራባዊያን ተቋማትና ታዋቂ ሰዎችን ማጋለጥ መጀመር ይኖርባቸዋል እንላለን። ለመነሻ ያህል የሚከተሉትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

1. ለወያኔ ሹማምንት የትምህርት ማስረጃ ሲያድሉ የቆዩት ምዕራባዊያን የትምህርት ተቋማት ዝርዝራቸው መታወቅ ይኖርበታል። ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ የሲቪክ ማኅበራት እነዚህ ተቋማት ከአምባገነን የኢትዮጵያ ገዢዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በአስቸኳይ እንዲያቋርጡ ማሳሰቢያ ሊጽፉላቸው ይገባል። ተቋማቱ አፋጣኝ ምላሽ ካልሰጡ የተቋሚቱን ተግባር ለተማሪዎቻቸውና ሌሎች ደንበኞቻቸው ማሳወቅ ይገባል። ይህ ዓይነቱ ተግባር የተቋማቱን ስም የሚያጎድፍ በመሆኑ ፈጣን ምላሽ እንደሚያስገኝ መገመት ይቻላል። በተለይም የብሪታኒያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሰሜን አፍሪቃ አምባገነኖች ጋር በነበራቸው የቢዝነስ ግኑኝነት ሳቢያ ቅሌት ውስጥ የገቡበት ጊዜ በመሆኑ የማጥቃት ርምጃው ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው፤ መፍጠን ይኖርብናል።
2. የከፋት ቁንጮ ከሆነው መለስ ዜናዊ ጋር ልዩ የጥቅም ወዳጅነት የፈጠሩ ታዋቂ ሰዎች በአውሮፓና አሜሪካ አሉ። አንዳንዶቹ (ለምሳሌ እንደ ጀፈሪ ሳክስ እና ቶማስ ስቲግሊክስ ያሉ) በሙያቸው ከበሬታን ያገኙ ሰዎች ናቸው። ሌሎች ደግሞ የፓለቲካ ሰዎች ወይም በጎ አሳቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከአምባገነኖች ጋር መሞዳሞድ የእነሱ የግል ክብር እና ሙያቸውን የሚያጎድፍ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ይህንን እንዲያውቁ እና ራሳቸውን ከመለስና ቡድኑ እንዲያርቁ በማያሻማ ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል። አለበለዚያ የራሳቸውን ክብር የሚያጡ መሆኑን ማሳሰብ ይገባል።
3. ከኢትዮጵያ አምባገኖች ጋር የኮንትራት ሥራ ሠርተው ገንዘብ የተቀበሉ ተቋማት "የደም ገንዘብ" ነክተዋልና ከኮንትራቱ ያገኙትን ትርፍ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲሰጡ ማስጨነቅ ይገባል። ቢዝነስ በስነምግባር መመራት አለበት። ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር የነገዱትን ሁሉ በሙስና የምንጠረጥራቸው በመሆኑ ራሳቸውን እንዲያጠሩ እንንገራቸው።
4. የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ቤተሰቦቻቸው በውጭ አገራት ውስጥ የሚያካብቱትን ሃብትና ንብረት መከታተል፤ ቤቶቻቸውን መያዝ፤ በንግዶቻቸው ላይ ማዕቀብ መጣል፤ በየሄዱበትና በየደረሱበት ማስነወር በተከታታይና በተደራጀ መልክ ሊሰራ የሚገባ ተግባር ነው።
5. በኢንተርኔትም የጥቃት ዘመቻ መጀመር ይኖርበታል። በፌስ ቡክ የተጀመረው ዘመቻ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ቢሆንም በቂ ነው ማለት አይደለም። ፌስ ቡክ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊዘጋ ይችላል ብሎ በማሰብ አማራጭ ሊፈለግ ይገባል። የኢንተርኔት አገልግሎት የሌላቸው ወገኖቻችንን እንዴት ልንደርሳቸው እንደሚገባም ሊጠና ይገባል።
6. በቴሌቪዥንና በሬድዮ የተጀመረው ዘመቻ በከፍተኛ ሁኔታ ማጠናከር ይገባል። ኢሳትን ማጠናከር የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ኃላፊነት መሆን ይኖርበታል።
7. በየአገሩ ኢትዮጵያዊያን የሚያደርጓቸው የተቃዉሞ ሰልፎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል።

ግንቦት 7 ጥቃቱን የተሳካ ለማድረግ የወጣቶች የፈጠራ ችሎታ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ እንደሚችል ከፍተኛ እምነት አለው። ወጣቶቻችን የትግራዩ ገዢ ጉጅሌን የመረጃ አፈና የሚበጣጥሱበት መንገድ አያጡም ብሎ ያምናል። ይህን የፈጠራ ችሎታ መጠቀሚያ ወቅት አሁን ነው።

በውጭ አገራት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ዓይኖቹን ከአገር ቤት ሳይነቅል ህዝባዊ አብዮቱን በያለበት አገር ዛሬውኑ ይጀምር!!! አሁን ማጥቃት ላይ ነን፤ በኅብረትና በጽናት እናጥቃ!!

**በቃ- ጋዮ!!!!**

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ ከወጣን ገና 10 ወራችን ነው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወያኔ ኢሃደግ በቅርቡ አድርጎት በነበረው የማስመሰል ምርጫ 99 6 % የሆነ የህዝብ ድጋፍ አግኝቻለሁ ብሎ በባዶ ሜዳ ይኩራራ የነበረው ዘረኛው መለስ እና ጀሌዎቹ፤ ላለፉት 20 አመታት በተደረገው ተመሳሳይ ምርጫ "የህዝብ ድጋፍና አመኔታ ሳይለየን ኖረናል" ይሉ በነበረው ታሪክ በማፈር የስልጣን ቆይታ ዘመናቸውን ወደ 10 ወራት ለማውረድ መገደዳቸው በሰሜን አፍሪካ ውስጥ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ በስነልቦናቸው ውስጥ ያሳደረው የመረበሽ ምልክት እንደሆነ ያለፈው ቅዳሜ ጋዜጣዊ መግለጫ ፍንትው አድርጎ አጋልጦታል ተብሎአል።

በኢሃደግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የመተካካት ፖሊሲ "ለመጪው 50 |ሃምሳ| አመታት ሥልጣን ይዘን ለመቆየት ምንም የሚያሰጋን የለም" ሲል ባዶ ጉራ በተሄደበት ይነዛ የነበረው የወያኔ ቁንጮ፤ "ህዝቡ የ5 አመት ኮንትራታችንን ከጨረስን ቦኋላ ካልተመቸነው በህገመንግስታችን መሠረት በምርጫ የሰጠንን ድምጹን በመንሳት በዚረራ ሊያባርረን ይችላል" ሲል ተደምጦአል። በምርጫ 97 ወቅት የአድስ አበባ ህዝብ ድምጹን ሙሉ በሙሉ ለቅንጅት በመስጠቱና ወያኔ በዚረራ በመሸነፉ ፤ በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ አጋዚ የተባለ ቅልብ ጦር ህፃንና ሽማግሌን ሳይለይ ከ200 በላይ ንፁሃን ዜጎችን በጠራራ ፀሃይ እንደጨፈጨፈ አይዘነጋም። ወያኔ በዝረራ በመሸነፉ ጥርስ የነከሰባቸው በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች አሁንም ቢሆን "የወቅቱን የሰሜን አፍሪካን ሁኔታ በመከተል የአደባባይ ነውጥ አያስኑም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው"ያለው ወንጀለኛው እና ነፍሰ ገዳዩ መለስ ዜናዊ "ይህንን የሚሞክሩ ከሆነ እንደከዚህ በፊቱ እነርሱን እያሰርን መልሰን በይቅርታ መፍታቱ እንደሰለቸን ሊያውቁና ሊታቀቡ አሊያም በህይወታቸው ላይ መወሰናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል" ሲል የዛቻ መል ዕክት አስተላልፎአል።

## ወያኔ ኢሳትን ከአየር ለማውረድ ከፍተኛ የሆነ ዘመቻ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከአሁን ቀደም ኢሳትን ከአየር ለማውረድ ከአረብሳት ጋር የጥቅም መመሳጠር ተፈጥሮ ነበር ያሉት ምንጮቻችን ለሶስት ወራት ያህል የኢሳትን ስርጪት ያስተላልፍ የነበረው ታይኮም የተባለው የሳታላይት ካምፓኒም በተደረገበት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጫናና ይህ ነው ተብሎ በትክክል ለመግለጽ በሚያዳግት የተለያየ መደለያ የስርጭት አገልግሎቱን አዳቋረጠ ማወቃቸውን ገልጸዋል። የዝግጅት ክፍላችን የደረሰውን መረጃ አስመልክቶ የኢሳት ማኔጅመንት አስተያየት እንዲሰጥ ተጠይቆ "ወያኔ እያደረገው ያለው ኢሳትን በተቻለ ፍጥነት ከአየር የማጥፋት ጥረት አሁን የተጀመረ አዲስ ክስተት እንዳልሆነ እናውቃለን; ።

ቀደም ሲል በአረብ ሳት እናስተላልፍ በነበርንበት ወቅት በውድ ዋጋ ከቻይና ተገዝቶ ሰሜን ኢትዮጵያ በተተከለ የሳተላይት መጥለፊያ መሳሪያ ይመቱት እንደነበረ መረጃ ነበረን ከዚያም ቦኋላ ታይኮም ላይ የነበረንን ስርጭት በዚያ መሳሪያ ለመምታት ተሞክሮ ባለመሳካቱ የቻይና ኤክስፐርቶች ጭምር ያሉበት አንድ ኮሚቴ በመለስ ዜናዊ ት ዕዛዝ ተቋቁሞ መፍትሄ ስላላስገኘ በሌላ መንገድ ካምፓኒው አግልግሎት መስጠቱን እንዲያቋርጥ አስደርገውታል ። ከዚያ ልምድ ባገኘነው ልምድ በማንኛውም ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ጥቃት ሊፈጸምብን ይችላል በሚል የተለያዩ አማራጮችን ታሳቢ በማድረግ እየተንቀሳቀስን ነው፤ ገንዘባችንን ይጭነቀው እንጂ እስከመጨረሻዋ የነጻነት ቀን ድረስ ገንዘብ የሚለግሱን እውነተኛ ኢትዮጵያዊያን እስካሉ ድረስ ጥቃቱን በመመከት በአጭር ጊዜ ወደ አየር ልንመለስ የምንችልበትን አቅም እያጎለበትን ነው" ብለዋል። በአገር ቤት ያሉ አድማጮቻችንም ይህንን አውቀው እንዲዘጋጁ መል ዕክት ማስተላለፍ ጀምረናል በማለት በወያኔ ግፊት ኢንቴል ሳት አገልግሎት ካቋረጠ በሌላ መንገድ ወደ አየር የመመለሱን እድል መኖር ገልጸልናል። አድማጮቻችን የግንቦት 7 ድምጽ በኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት እንዲኖር የሚንናፍቅ ሁሉ ኢሳትን በገንዘብ የመርዳት ጊዜው አሁን መሆኑን ያሳስባል።

## ወያኔ የሰሜን አፍሪካን አይነት አብዮት በኢትዮጵያ ውስጥ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለማወቅ እንዳልተቻለ ለመረዳት ተችሎአል። እንደሁለቱ የኦሮሞ ድርጅቶች መረጃ በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች ተመሳሳይ ማዋከብና እንግልት እየተፈጸመባቸው እንደሆነ ይህም ወያኔ በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየፈጸመ ካለው ተከታታይ የጥቃት እርምጃ አንዱ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል። በሰሜን አፍርካ እና መካከለኛው ምስራቅ እየተካሄደ ያለው ህዝባዊ አብዮት መለስ ዜናዊን ምን ያህል እረፍት እንደነሳው የቱንዚያው አይነት አብዮት ይነሳብናል ብዬ ሳስብ ላአድርም በማለት ያደረበትን ስጋት ከፍተኛነት በተዘዋዋሪ ገልጾአል ባለፈው ቅዳሜ ጋዜጣዊ መግለጫው።

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር በ1996 ዓ.ም ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረበ (በዶ/ር ታደሰ ብሩ)

### ጽሁፉ የያዛቸው በርካታ ቁም ነገሮች ስላሉ በዚህ ጋዚጣ በተከታታይ ለማቅረብ ችለናል (ክፍል 1)

1. ***መግቢያ***

ክቡራትና ክቡራን!

በዛሬዉ ምሽት በዚህ መድረክ «ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት»ን በተመለከተ ለአገራችን ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያለኝን ምኞት፣ ስጋትና ተስፋ ለእናንተ ክብራትና ክቡራን እንዳቀርብ የጋበዘኝን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ከልብ አመሰግናለሁ::

ይህ ርዕስ ለዉይይት የቀረበበት ወቅት ብሔራዊ ምርጫ የተቃረበበትና በእኔም በብዙ ኢዮጵያዊያን ወገኖቼ ይህ ምርጫ ከዚህ በፊት ከነበሩት ይበልጥ የአገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል የሚል ግምት መኖሩ ለዛሬዉ ዉይይት ጥሩም፣ መጥፎም፣ አጋጣሚ ነው:: ጥሩነቱ ርዕሱ ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ጋር መያያዙ ሲሆን ክፋቱ ደግሞ የምርጫው መቅረብ ሁላችንንም የበለጠ ወገንተኛ /partisan/ ያደርገናል፤ እናም ገለልተኛ የሆነ ውይይት ማድረግ ይከብደን ይሆናል ብዬ ሰግቻለሁ::

የተከበራችሁ ታዳሚዎች! በዛሬዉ ዕለት «ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት» በሚል ርዕስ የራሴን እጅግ ዉስን የሆነዉን ግንዛቤዬን ለዉይይት ሳቀርብ ስለርዕሱ ከኔ የበለጠ እዉቀት ያላቸዉ ሰዎች እዚህ አዳራሽ ውስጥ መኖራቸውን እያወቅሁ ነዉ:: በመሆኑም የማቀርበዉ አስተያየት ለዉይይት መነሻነት ታገለግል እንደሆን እንጂ ርዕሱን በብቃትና በጥልቀት ትዳስሳለች ብዬ በማመን አይደለም::

ንግግሬን ፈር ለማስያዝ በሚከተለዉ አኳኋን ሸንሸኘዋለሁ:: በቅድሚያ «ሰላም»፣ «ዲሞክራሲ» እና «ልማት» ስል ምን ማለቴ እንደሆነ በአጭሩ ከገለፅኩ በኋላ እነዚህ ሶስት መልካም ነገሮች በአንድ አገር በአንድነት እንዲገኙ መሟላት አለባቸዉ ብዬ የማምንባቸዉን ሁኔታዎች ለመዳሰስ እሞክራለሁ:: ቀጥሎ ደግሞ እነኚህ ሶስት መልካም ነገሮች እኔ በተረዳሁት መጠን ዛሬ በኢትዮጵያችን ዉስጥ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ከገለፅኩ በኋላ ዛሬ ማድረግ ያለብንን ነገሮች ከከወንን የ2020ዋ ኢትዮጵያ አገራችን ልትደርስበት ትችላለች ብዬ የማምነዉና እንድትደርስም አጥብቄ የምመኘዉን ደረጃ ለማየት እሞክራለሁ::

2. **ትርጓሜ**

አንዳንድ ደጋግመን የምንጠቀምባቸዉ ቃላት በጣም አšሚ የሆነ ትርጉም ያላቸው መሆኑ የሚገርም ነው:: ከእነዚህ ቃላት አንዱ «ሰላም» ነዉ:: ሰላምን ለማደፍረስ የሰላም አጀንዳ ማንገብ እየተደጋገመ መምጣቱ የሰላም ትርጉም ምንኛ የተዛባ መሆኑን ያመለክታል ብዬ አስባለሁ:: አዶልፍ ሂትለርም በርካታ የሰላም ጥሪዎችን አድርጓል:: በአንድ ወቅት የሶማሊያው መሐመድ ዚያድ ባሬ የሰላም ሰልፍ መርተዋል:: የዩጋንዳው ማርšል ኢዲያሚን ዳዳም ራሳቸዉን የሰላም መከታ አድርገው ሲቆጥሩ ኖረዋል፤ ኒšንም ተሸልመዋል:: እኛም አገር የነበሩና ያሉ መንግሥታት ሁሉ ራሳቸውን የሰላም ጋሻ ጃግሬ አድርገው ሲቆጥሩ ኑረዋል:: እነዚህ ሁሉ አገራት ግን ሰላም የተናፈቀባቸው ነበሩ:: ለአንዳንዱ «ሰላም» ተቀናቃኞችን ደምስሶ ከጨረሱ በኃላ የሚጣሉት የሌለበት ሁኔታ ማለት ነው፤ ለአንዳንዱ ደግሞ በፍርሃትና ዝምታ መገዛት ማለት ነው:: ለሌሎች ደግሞ «ሰላም» ማለት መቻቻልና መደራደር ማለት ነው:: በሁሉም ትርጓሜዎች «ሰላም» የአመፃና ሽብር አለመኖርና ቀጣይነቱን ያመለክታል:: ለዛሬዉ ዉይይት እኔም ይህንን ቀላል ትርጓሜ ማለትም የአመፃና ሽብር አለመኖርን እጠቀማለሁ፤ ሆኖም የማተኩረዉ በአገር ውስጥ ሰላም /domestic peace/ ላይ ብቻ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ:: ዓለም-ዓቀፍ ሰላም በአገር ውስጥ ሰላም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢኖረውም በዋነኛነት የሚወሰነው በአገር ውስጥ ሁኔታዎች ነው ብዬ አምናለሁ::

ሌላው አወዛጋቢ ቃል «ዲሞክራሲ» ነው:: በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት መንግሥታት ራሳቸውን «ዲሞክራሲያዊ» ብለው ያወጁ ናቸው:: ምርጫ ፈጽሞ የማይካሄድባቸው ሀገራት ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው:: በዲሞክራሲ ስም አምባገነን ሥርዓት መዘርጋት ፋሽን ከሆነ ሰንብቷል:: የነባሮቹ ዲሞክራሲያዊ አገሮች ተግባርም ከአምባገነኖቹ መለየት አስቸግሯል:: በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይሆን ይሆናል «ዲሞክራሲ የሚባል ነገር በዓለም ላይ የለም» ዓይነት አስተያየቶች ከተማሩ ሰዎች አንደበት ሲነገር የምንሰማው:: አንዳዶቹማ «እውን አሁን ከምር አሜሪካ ውስጥ ዲሞክራሲ አለ?» «እዉን እንግሊዝ ውስጥ ዲሞክራሲ አለ?» … ወዘተ እያሉ «ያፋጥጡናል»:: ሰዎች እንዲህ ዓይነቱ ምፀታዊ ድምዳሜ ላይ የሚደርሱት ዲሞክራሲን በውጤቱ መመዘን ስለሚፈልጉ ይመስለኛል:: እነዚህ ሰዎች ያልተረዱት ወይም ሊረዱት ያልፈቀዱት ዲሞክራሲ የአስተዳደር ሥርዓት መሆኑን ነው:: በዚያ አልፎ የሚመጣው ዉጤት ሳይሆን ሥርዓቱ ነው ዲሞክራሲያዊ ነው ወይም አይደለም የሚባለው:: ዲሞክራሲ ከሌሎች የአስተዳደር ሥርዓቶች ሲወዳደር መልካም ውጤቶችን ለማስገኘት የተšለ አማራጭ ነዉ ተብሎ ይታመናል:: ይህ ዕምነት ግን ሁሌ ዕዉነት ላይሆን ይችላል:: ውጤቱ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሥርዓቱ ዲሞክራሲያዊ ከሆነ ዲሞክራሲያዊ ነው::

ዲሞክራሲ ሥልጣንና ኃላፊነት የዜጎች የሆኑበት እያንዳንዱ ዜጋ ደግሞ ይህንን ሥልጣንና ኃላፊነት በቀጥታ አሊያም በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮቹ አማካይነት በተግባር ላይ የሚያውልበት ሥርዓት ነው:: ዲሞክራሲ የነፃነት መዋቅር ነው::

ለዲሞክራሲ መስፈን በርካታ መዋቅራዊ ሁኔታዎች መሟላት ያለባቸው ሲሆን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ የአብላጫዎች መሪነትና የውሁዳን ብዙሃን የመሆን መብት መረጋገጥ፤ የጦር ሠራዊቱ በሕዝብ በተመረጠ ሲቪል አስተዳደር ሥር መሆን፤ የፖለቲካ ፖርቲዎች በነፃነት መደራጀትና መንቀሳቀስ፤ የነፃና ፍትሃዊ የፖለቲካ ፍክክርና ምርጫ መኖር፤ የዳበረ ነፃ ፕሬስና ሚዲያ መኖር፤ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ያለው መንግሥት መኖር፤ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ያለው የሕግ አውጭ አካል መኖር፤ ከፖለቲካ ነፃ የሆነ የፍርድና ፍትህ ሥርዓት መስፈን ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

የእነዚህና መሰል መዋቅሮች መዘርጋትና ተግባር ላይ መዋል ነው አንድን የአስተዳደር ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ የሚያደርገው እንጂ ይህንን ሥርዓት አልፎ የመጣውን ውጤት ጥሩነት አይደለም:: ለዚህም ነው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች አንዳንዴ ኢ-ፍትሃዊ ተግባር ሲፈጽሙ እንኳን ዲሞክራሲያዊነታቸዉን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ተገቢ የማይሆነው::

እንደ «ሰላም» እና«ዲሞክራሲ» ባይሆንም «ልማት» የሚለውም ቃል አሻሚ ነው:: እዚህ ላይ አንድ ቀልድ እንድናገር ይፈቀድልኝ:: በሽርሽር ላይ የነበሩ የመንግሥት የኢኮኖሚ አማካሪዎች መንገድ ጠፍቶዓቸው ከባዘኑ በኃላ ዋናዉ ኢኮኖሚስት «እስቲ ካርታውን ወዲህ በሉ» ብሎ ካርታውን ተቀብሎ ዘርግቶ በጥንቃቄ ከለካ በኋላ በታላቅ የድል አድራጊነት ስሜት «የት እንዳለን በትክክል ደርሼበታለሁ! ይታያችኃል እዚያ ማዶ ያለው ተራራ! አናቱ ላይ ነው ያለነው» አለ ይባላል:: ይህንን ቀልድ የአፍሪካ መንግሥታት በተደጋጋሚ ይቀልዱታል:: ማደጋችንና መሻሻላችንን ይነግሩናል፤ እኛ ደግሞ አልታይ፣ አልገባ እያለን እንቸገራለን:: በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የ«ልማት» ትርጉም ቢጠፋብን አይፈረድብንም:: ልማት መለካት የሚቻልና መለካትም ያለበት ነዉ:: የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ የማይሸተት፣ የማይቀመስ «ልማት» ልማት ነው ብዬ አልገምትም:: በቁጥሮች አጠቃቀምና ትርጓሜ ላይ ጥንቃቄ ሳናደርግ «ቁጥሮች እንደሚያመለክቱት በፍጥነት እያደግን ነዉ፤ ይህ ደግሞ በእርግጥም መልማታችንን ይመሰክራል» ማለት ከራሱ በላይ ካርታዉ በማመን እዚያ ማዶ ያለዉ ተራራ ጫፍ ላይ ነው ያለነው እንዳለዉ የቀልዱ ኢኮኖሚስት መሆን ነው:: በእኔ እምነት ልማት የሕዝቡን የዛሬ ኑሮ እና/ወይም የነገ ተስፋውን በተጨባጭ መለወጥ አለበት:: ይህም በአመጋገባችን፣ በጤናችን፣ በአለባበሳችን፣ በትምህርታችን፣ በአኗኗራችን፣ በአስተዳደራችን፣ እየተššለ መምጣት መገለፅ አለበት:: ልማት ደግሞ ከራስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ጋርም መነፃፀር አለበት:: ሶቭየት ኅብረትና አልባንያ በከፍተኛ ፍጥነት እየለማን ነው እያሉ ራሳቸውን ሲሸነግሉ ቆይተው ዓይኖቻቸውን ገልጠው ጎረቤቶቻቸውን ሲመለከቱ የደረሰባቸውን የስነልቦና ውድቀት ልብ ይሏል::

«ልሂቃን» የሚለዉም ቃል አሻሚ ነዉ:: ልሂቃን መንፈሳዊ እና/ወይም ዓለማዊ ኃይል ባላቸው ቡድኖች፣ ማኅበራትና ተቋማት ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ ተሰሚነት ምክንያት የግል ውሳኔያቸው በሀገሪቱ አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል:: ይህም ማለት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በሳይንስ፣ በምርምር፣ በወታደራዊ ጉዳዮች፣ በሃይማኖቶች፣ በሙያ ማኅበራት፣… ወዘተ መስኮች ተደማጭነት ያገኙ - አብዛኛውን ጊዜ አመራሩንም የያዙ - ሰዎችን ያመለክታል:: የፖለቲካ ልሂቃን፣ የኢኮኖሚ ልሂቃን፣ ወታደራዊ ልሂቃን፣ የምሁራን ልሂቃን፣ የሃይማኖት ልሂቃን፣ የትምህርት ልሂቃን፣ የባህል ልሂቃን፣ … ወዘተ እያልን ብሔራዊ ልሂቃንን ከፋፍለን እያንዳንዱን በተናጠል ልናጠናው ብንችልም ሁሉንም የሚያስባስባቸው አንድ የጋራ ባሕሪይ ግን ከላይ እንደተገለፀው የግል ሃሳባቸውና ውሳኔያቸው ፈጣን የሕዝብ ድጋፍን በማስገኘት በአገሪቱ አጠቃላይ ፖለቲካ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል መሆኑ ነው:: እነዚህ ግለሰቦች በእንግሊዝኛ ቋንቋ «ኤሊት» የሚባሉት ሲሆኑ ትክክለኛ የአማርኛ አቻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ባልሆንም ከአቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በመዋስ «ልሂቃን» የሚለዉን ቃል እንድጠቀም ፍቀዱልኝ:: ልሂቃን ከጠቅላላው ሕዝብ አንፃር ሲታዩ ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ ነው::

«ፖለቲካ የተቀነባበረ የቡድን ፍላጎት መግለጫ ነው:: አንድ የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል የተለየ ፍላጎት ካለው ያንን የሚያስፈፅም የፖለቲካ ድርጅት ይነሳል:: ግለሰብ ታጋይ ይነሳል፣ ይወድቃል፣ ይለወጣል፣ ይሞታል፣ ያ የሕዝብ ፋላጎት እስካልረካ ድረስ ግን ትግሉ ይቀጥላል:: በመሆኑም የአንድ አገር ፖለቲካ የሚወሰነዉ ባሉት የተለያዩ ማኅበራዊ ፍላጎቶችና ቅራኔዎች እንጂ በግለሰቦች አይደለም» የሚል ክርክር እንደሚነሳ አውቃለሁ:: ሆኖም «የሕዝቡን ፍላጎቶች» በቅድሚያ የሚገነዘቡት፣ ሕዝቡንም ስለ «ፋላጎቶቹ» የሚያስረዱትና ለትግል የሚያንቀሳቅሱት ግለሰብ ልሂቃን ናቸው፤ በኋላም ትግሉን የሚመሩት እነሱው በመሆናቸው የክርክሩ ጭብጥ «አልሸሹም ዞር አሉ» ነው::

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## የአፍሪካ ህብረት ያደረገው የመሪዎች ስብሰባ ጉልህ እርምጃ ሳይወስድ ተጠናቀቀ

ሃሙስ የካቲት 30 ቀን በአዲስ አበባ በተደረገው 265ኛ የአፍሪካ የሰላምና ጸጥታ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ የተሳተፉት የአፍሪካ መሪዎች በሰሜን አፍሪካይቱ አገር በሊቢያ እየተፈጸመ ያለውን ጭፍጨፋ በጠነከረ ቋንቋ ለማውገዝና ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ ለመጠየቅ የሚያስችል ወሳኔ ሳያስተላልፍ መጠናቀቁን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

ዲሞክራት ነን እያሉ በአያለ የአፍሪካ ቢጤዎቻቸው ሲሞካሹ የነበሩት የቱንዚያው ቤን አሊንና የግብጹ ሙባረክ በህዝባዊ ተቃውሞ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ከመገደዳቸው በፊት የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለመቀልበስ ይቆጣጠሩት በነበረው የጸጥታ ሰራተኞች በዜጎቻቸው ህይወት ላይ የመግደል ወንጀል ሲፈጽሙ ምንም አይነት ተቃውሞ ያላሰማው የአፍሪካ ህብረት፤ በሁለቱ አገሮች ውስጥ የተደረገው ለውጥ ወደሌሎች አገሮች እንዳይዛመት ከመስጋት ይመስላል እስከዛሬ ድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ድምጽ ሳያሰማ ቆይቶአል። በቅርቡ የአህጉር ድርጅቱ ሊቀመንበር የነበሩት ሞአመድ ጋዳፊ የ42 አመት የአገዛዝ ዘመናቸው እንዲያበቃና በአገራቸው የመንግሥት ለውጥ እንዲኖር የሚጠይቀውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለመደፍጠጥ ከፍተኛ የሆነ የታጠቀ ሃይል በምድርና በሰማይ ያሰማሩ ቢሆንም ይህንን እርምጃ በግልጽ ለማውገዝና እንዲቆም ለማድረግ ምንም አይነት የጸና አቋም አለመውሰዱ የምዕራባዊያን መገናኛ ብዙሃን መዘባበቻ አድርጎታል። በመሪዎቹ ስብሰባ ላይ የጋዳፊን እድሜ ለማራዘም ከፍተኛ ገንዘብ በመቀበል ነፍሰ ገዳይ ወታደሮችን ወደ ሊቢያ የላኩ አገር መሪዎች ጭምር የተገኙ ሲሆን ለሥልጣን ሲሉ የበርካታ ንጹሃን ህይወት በመቅጠፍ የሚታወቁ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቶቹ በዚያ የአህጉር ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ መገኘት የተለሳለሰ አቋም እንዲያዝ ዋና ምክንያት ይሆናል የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ።

ያለ ህዝባቸው ፈቃድና ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ስልጣን ማማ ላይ ተቆናጠው የአገራቸውን እና የህዝባቸውን ሃብት በመበዝበር የሚታወቁ ፤ በሙስና የተጨማለቁና የዜጎቻቸውን መብት በመርገጥ የሚታወቁ በርካታ መሪዎችን የተሸከመቺው አህጉራችን አፍሪካ ከ1955 ጀምሮ አንድ የጋራ የሆነ አህጉራዊ ድርጅት ይኑራት እንጂ በዚህ አህጉራዊ ተቋማ አማካይነት እስከ ዛሬ ያስመዘገበቺው እድገት ወይም በአህጉሪቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ የለም። ቀደም ሲል የአፍሪካ አንድነት ቆየት ብሎ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት የተባለው ይህ ተቋም በማ ዕቀፉ ውስጥ ያሉ አገሮች መሪዎች የዜጎቻቸውን መብት ሲረግጡ፤ ዜጎቻቸውን ሲገድል፤ ሲያስሩና የተለያየ ዘግናኝ ሰቆቃዎች ሲፈጸሙ ምንም አይነት ተቃውሞ በማሰማት የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ በምርጫ ሽፋን የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም የምርጫ ድራማ የሚያዘጋጁ አገሮችን ላይ በምርጫ ታዛቢነት ሥም እየዞረ የተጭበረበረውና የተዘረፈው የመራጭ ድምጽ እንዳይታወቅ ከገዥው ወገን ጋር በመወገን ምስክርነት በመስጠት እና ሥልጣን ላይ ያሉት ደግመው ደጋግመው እንዲገዙ ረጅም ዕድሜ በማሰጠት ይታወቃል። በምርጫ 97 በአገራችን ተደርጎ የነበረውን ምርጫ የአውሮጳ ህብረትና የካርተር ማዕከል ከፍተኛ ማጭበርበር የተፈጸመበት መሆኑን ሲያጋልጡ የዚህ ተቋም ታዛቢዎች ግን ለአፍሪካ አረአያነት ያለው ምርጫ ተካሁዶአል በማለት እንዳወደሱት ይታወሳል።

## በነዳጅ ላይ የተደረገው የዋጋ ጭማሪ ህዝብ እንዳያስቆጣ ወያኔ መለማመጥ ይዞአል

የዜረኛው ወያኔ አገዛዝ በነዳጅ ላያ ያደረገው ጭማሪ ህዝቡን ለአመጽ እንዳያነሳሳ በአስቸኳይ የዋጋ ማሻሻያ እንደሚያደርግ እና የዋጋ ንረቱን ለማረጋግት እየሠራ መሆኑን ነጋ ጠባ በፕሮፖጋንዳ ማሰራጫዎቹ የመገናኛ ብዙሃን እያስተላለፈ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ለህዝብ ካለው ንቀት የተነሳ እንዳሻው ህዝብን በመዝለፍ የሚታወቀው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የተጠራቀመ የህዝብ ብሶት ገንፍሎ መውጣቱ እንደማይቀር ከሰሜን አፍሪካው ህዝባዊ አብዮት ልምድ እየቀሰመ በመምጣቱ እስከ ዛሬ በነበረው የ20 አመት አገዛዝ ታይቶ የማይታወቅ ህዝባዊ ወገንተኛነት ለማሳየት ደፋ ቀና እያለ እንደሚገኝ ለሥር ዓቱ ቅርብ የሆኑ ምንጮች ለግንቦት 7 ዘጋቢ ገልጾዋል። ቀደም ሲል የወያኔ ፓርላማ ተሿሚዎች ታማኝነታቸውና ታዛዥነታቸው ለህወሃት ጌቶቻቸው ብቻ እንዳልነበረ ዛሬ ዛሬ ይወከላሉ ወደሚባሉባቸው የምርጫ ተብዬ ጣቢያዎች ድረስ ተጉዘው ህዝብ እንዲያነጋግሩና ችግራቸውን እንዲያዳምጡ ከመላክ ጀምሮ በሰበብ አስባቡ ያለ አግባብ ከሥራ የሚሰናበቱ የመንግሥት ሠራተኞችን ልብ ለማማለል ከአሁን ቦኋላ ማንም ሰው ከሥራ ላይ እንደማይቀነስ ፤ ደመወዝ ፤ እድገትና የነፃ ትምህረት ዕድል ለሁሉም እንደሚመቻች ባዶ ተስፋ እየተገባ እንደሆን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከተለያየ ቦታ ያሰባሰባቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ ገልጾአል።

ወያኔ በተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲው የፈጠረውን የኑሮ ውድነት በነጋዴው ህብረተሰብ ላይ ለማላከክ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ከወያኔ የጅምላ ንግድ ድርጅቶች በውድ ዋጋ የገዙትን የፍጆታ ዕቃዎች ከገዙበት ዋጋ በታች ቀንሰው እንዲሸጡ የዋጋ ተመን አውጥቶ የነበረ ሲሆን እነኚያ የዋጋ ተመን የታወጀባቸው የፍጆታ ዕቃዎች ከገቢያ ላይ ጨርሶ የጠፉ መሆናቸውን ዘጋቢያችን በላከልን ዜና አረጋግጦአል።

## የአውሮጳ ፓርላማ የኢትዮጵያን ጉዳይ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ማአይስት ፈለግ የሚከተለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በ እርዳታ የሚያገኘውን ገንዘብ ለፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ እንደሚጠቀምበት በተለይ ደግሞ በሰፍቲ ኔት ለታቀፉትና ምግብ ለሥራ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉት ሁሉ ዋና መስፈርቱ ለወያኔ ፖለቲካ ታማኝነት ወይም አባልነት በመሆኑ ይህ የ እርዳታን ገንዘብ አለአግባብ ከመጠቀም አልፎ ከሰብ ዓዊ መብት ጥሰት ጋር የሚቆራኝ ነው ብለዋል። የወያኔ ባለስልጣኖች የምዕራብ ለጋሾችን ለማማለል ስለዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት አያያዝ ወገንተኝነታቸውን በመግለጽ የማይታሙ በተግባር ግን ኮሚንስታዊ የስልጣን ማዕከላዊነት በመዘርጋት ከላይ እስከታች ቀበሌ ድረስ ያሉትን መዋቅሮች የሚቆጣጠሩ ኮሚንስት አምባገነኖች ናቸው ሲሉ ነቅፈዋል። የሂውማን ራይትስ ዎች ተመራማሪ የሆኑት ሚስተር ራወለንስን ላቀረቡት ሪፖርት ማስተባቢያ ያቀረበው በቅርቡ በቤልጅዬም የወያኔ ኤምባሲ አንደኛ ጸሃፊ ሆኖ የተመደበ ግለሰብ የሂውማን ራይትስ ሪፖርት ከበስተጀርባው የፖለቲካ አጀንዳ ያለው አክራሪ የሆኑትን የአገሪቱን ተቃዋሚዎች ጩሄት እንዳለ ተቀብሎ የሚያስተጋባና ወያኔ እያስመዘገበ ያለውን ዕድገት ለማሰናከል እርዳታ እንዳይሰጥ የሚከላከል ነው በማለት ከውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ተጽፎ የተላከውን 2 ገጽ ጽሁፍ በ7 ደቂቃ ንባብ አሰምቶአል።

የአውሮፓ ግብር ከፋዮችን ገንዘብ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለሚፈጽሙ አምባገነን የአፍሪካ አገር መሪዎች የሚደለድለው የአውሮፓ ኮሚሽን ተወካይ በበኩሉ በአድስ አበባ የሚገኙ የለጋሽ አገር ተዋካዮች ቡድን ሂውማን ራይትስ ዎች ያቀረበውን ክስ በማስርጃ ለማስደገፍ እንዳልተቻለ መግለጫ ማውጣታቸውን እንደአስረጂነት በመቆጠር፡ የምዕራቡ አለም በአመት 3 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ መስጠት ከመጀመሩ ከ15 አመት በፊት ለኢትዮጵያ ተረጂዎች በአመት እስከ 700 ሺ ቶን እህል ይለገስ እንደነበረ ገልጸው ያቁጥር ዛሬ ወደ 400ሺ ቶን ወርዶአል በማለት ወያኔ በ15 አመት ጊዜ ውስጥ ከ700 ሺ ቶን እርዳታ ተቀባይነት ወደ 400 ሺ ቶን መውረዱን እንደመሻሻል ገልጸዋል። በአገራቸው የሞርጌጅ ዕዳ መክፈል ፋታ የነሳቸውና ኢትዮጵያን ወደ መሰለች አገር ተልከው በዘረፋና ሙሲና ከተጨማለቁት አምባገነኖች ጋር የሚተሻሹ የምዕራብ ተወካዮች ወያኔ የሚፈበርከውን የዕድገት ቁጥር ሲያስተጋቡ ከሰነበቱ ቦሃላ 45 ቢሊዩን የሚጠጋ ገንዘብ በዕርዳታ በተሰጠበት 15 አመት እድሜ የዕርዳታ ምግብ ለምን መቀበል እንዳስፈለገ ከመጠየቅ ይልቅ በግማሽ ያህል እንኳን ያልቀነሰውን ቁጥር አድንቀው ሲናገሩ ማስተዋል ስብሰባውን ለመከታተል በአዳራሹ የተገኙትን ኢትዮጵያዊያን አስገርሞአል።

የሂውማን ራይትስን ዎች ለማጣጣል ከአዲስ አበባ ተጽፎ የተላከው ደብዳቤ ፡ክብርት አና ጎመዝን የኢትዮጵያን ህዝብ ብሶት በየሄዱበት ከማስተጋባት እንዲቆጠቡ ከአሁን “ቦኋላ የመንግሥታችን ትዕግስት ከጣራው በላይ ሂዶአልና ይጠንቀቁ ” ሲል አስጠንቅቆአል። ማስጠንቀቂያውን የሰሙ አንድ የፓርላማው አባል የኢትዮጵያን ህዝብ ማሸማቀቅ አንሶባችሁ የተከበሩትን እና የሚያደርጉትን ጠንቅቀው የሚያውቁትን የፓራላማችን አባልን ለማስጠንቀቅ መሞከራችሁ ድፍረት ብቻ ሳይሆን ጥጋብ ነው ካሉ ቦኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደቱኒዚያው ህዝብ ለመብቱ የሚነሳበት ቀን ከፊት ለፊታችሁ መሆኑን ልትገነዘቡት ይገባል በማለት የወያኔ መል ዕክት ለማስተላለፍ የመጡትን ተላላኪዎች አስገንዘበዋል።

## ዶ|ር ብርሃኑ ነጋ ዓለም ለአምባገነኖች ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ዶ|ር ብርሃኑ በዚህ የአውሮፓ ጉዞአቸው ያተኮሩበት የውይይት ሃሳብ የአምባገነኖችን ባህሪ አስመልክቶ ማወቅ ስለሚገባን ነገርና ለዚህም ልንወስደው ስለሚገባ ልምድ የሚዳስስ እንደነበረ ሮፖርተራችን ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል። የአምባገነኖች ባህሪያት በአብዛኛው የሚመሳሰል ቢሆንም አንድ አይነት እንዳልሆኑ ታይቷል ያሉት ዶር ብርሃኑ ቤን አሊ ህዝቡና ወታደሩ እንደከዳው ሲያውቅ በጊዜ በመሸሹና ቢያንስ እንደሌሎቹ አጥፍቶ መጥፋትን ከሚያስቡ አምባገነኖች አንጻር ሲታይ መልካም ሊባል እንደሚችል፣ ሆስኒ ሙባረክ ከቤን አሊ በባሰ መልኩ ስልጣኔን ከለቀቅሁ ግብጽ ርስ በርስ ትጋጫለች የሚል አምባገነን ስለነበር ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከስልጣን አልወርድም ብሎ በመቆየቱ ጥፋት መድረሱን፣ ቅሌቱ ግን ከቤን አሊ የባሰ እንደነበር ፤ የየመኑ አሊ አብደላህ በባሰ መልኩ የሲቪል ጦርነት እንዲነሳ የሚችለውን እያደረገ በመሆኑ ይህም የጥፋቱን መጠን ከፍተኛ እንደሚያደርገው፣ እንዲሁም ጋዳፊ እኔን ያልወደደ ሊቢያዊ አይደለም ብሎ እስከማመን በመድረሱ ከሁሉም የከፋ አምባገነን እንደሆነ ገልጸዋል፣ ፤

ስለ አምባገነኖች የአእምሮ በሽተኛነት ከጋዳፊ የበለጠ ገላጭ ነገር የለም ያሉት ዶ|ር ብርሃኑ ፤ የጋዳፊ መጨረሻ እስካሁን ከታዩት አምባገነኖች የከፋ እንደሚሆን በዚህም ምክኒያት የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከነጻነት ናፋቂው ህዝብ ጋር መቆም ግድ እንደሆነበትና ፤ ዓለማችንም እንዲህ እንዳሁኑ በአምባገነኖች ላይ ሲተባበር ታይቶ እንደማይታወቅ ገልጸዋል፣ ፤ አያይዘውም አብዮቱ በዓለም ህዝብ ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን ፤ አብዮቱ አድማሱን እያሰፋ መሆኑን ፤ በዚህም ምክንያት በተለይ ቻይናዊያን በሃገራቸው አመጽ እንዳይነሳ በሚል በሙሉ ሃይላቸው እየሰሩ መሆኑን ፤ የደቡብ ኮሪያ ወጣቶች ለሰሜኖቹ ወንድሞቻቸው ስለሰሜን አፍሪቃው አብዮት የሚገልጹ ጽሁፎችን በፊኛ (ባሉን) እየጻፉ መላካቸውን ፤ በአንዳንድ የአፍሪቅ ሃገራት አካባቢ ማስፈራሪያ እስከመሆን መድረሱን፣ በዚህም ምክንያት ዓለም ለአምባገነኖች የነበረው ትእግስት አልቆ እንጥፍጣፊው ብቻ የቀረ መሆኑን በስፋት ገልጸዋል።

ዶ|ር ብርሃኑ ነጋ በንግግራቸው መጨረሻ ኢትዮጵያዊያን ከሰሜን አፍሪቃው አብዮት ምን ትምህርት መቅሰም እንደሚኖርብን በስፋት የዘረዘሩ ሲሆን በሁለቱም አገሮች በተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ ቁጥሩ ከምንጊዜውም በላይ የሆነ ኢትዮፕያዊ መገኘቱን ለማወቅ ተችሎአል።

## የአዲስ አበባ አውራ መንገዶችና አደባባዮች ... (ከገጽ 1 የዞረ)

የተረጋገጠበት የመንግሥት አስተዳደር በአገራችን አለ፤ የሃብት ክፍፍልም ቢሆን አብዮት ከተቀሰቀሰባቸው አገሮች በተሻለ ሁኔታ በአገራችን ፍትሃዊ ነው በማለት መሳቂያና መሳለቂያ የሆነ ፕሮፖጋንዳ መንዛት ጀምሮአል ተብሎአል።

በምርጫ ህግ ሰላማዊ የሆነ የሥልጣን ሽግግር የሚደረግበትን መድረክ አመቻቻለሁ በማለት በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነጻ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ወያኔ በፈቀደበት ምርጫ 97 ከደረሰበት ሽንፈት ያገኘው ልምድ መልካም ስላልሆነ ወያኔ በምንም አይነት ህዝቡን ማመን ስለማይችል የአሁኑ መንገዶችን በፖሊስና በፀጥታ ሃይል ማጠር ምንጩ ያለፈው ልምዱ የፈጠረበት ስጋት ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው። ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ ቅድመ ምርጫ 97 የነጻ ካናቴራና የገንዘብ ጉርሻ ተሰጥቶት ሚያዚያ 29 ቀን መስቀል አደባባይ ለወያኔ ድጋፍ ወጥቶ የነበረው የአዲስ አበባ ነዋሪ በማግሥቱ ሚያዚያ 30 ቀን ተቃዋሚዎች ጠርተውት በነበረው ሰልፍ ላይ ያንኑ የወያኔ ካናቴራውን ለብሶ " ትናንት ለ እንጀራችን ዛሬ ለነፃነታችን " የሚል መፈክር እያሰማ በመውጣቱ እና በምርጫውም ወቅት ወያኔን ጉድ በማድረጉ ወያኔ ክፉኛ ቆስሎአልና ሰው አያምንም ይላሉ። የምርጫ 97 ን ወጤት ለመስረቅና ሥልጣን ላይ ለመቆየት ወጣቱን አደገኛ ቦዜኔ የሚል ቅጽል ሰጥቶ በአጋዚ ጦር በጠራራ ፀሃት በርካቶችን እንዳስገደለና እንዳቆሰለ የሚታወቅ ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org